# HIV – በደንብ ቁጥጥር የተደረገበት የ HIV ህክምና ውስጥ ያለ የታካሚ መረጃ

## የተዛማጅ በሽታ መረጃ መግለጫ

### ይህ መረጃ ለምን ተሰጥዎት?

በአንቲ-ሬትሮቫል መድሃኒቶች እየታከመ ያለ HIV ኢንፌክሽን አለዎት እና ሃኪምዎ የእርስዎን ህክምና በደንብ ቁጥጥር የተደረገበት ብሎ ገምግሟል። በደንብ ቁጥጥር የተደረገበት የ HIV ህክምና ማለት፡

- በሁሉም ጊዜ በደምዎ ውስጥ ያለው የቫይረስ መጠን ማወቅ አይቻልም።
- እንደታዘዘልዎ መድሃኒትዎን በአግባቡ መውሰድ አለብዎ።
- ቋሚ ህክምናዎችን እና የህክምና ቀጠሮዎች ላይ ይገኛሉ፣ ይህም በሃኪምዎ እንደታዘዘው በአመት ከ 2-4 ጊዜ ነው።

### HIV ምንድነው?

HIV ማለት በሽታ የመከላከል አቅምዎን የሚጎዳ ቫይረስ ነው። ዛሬ፣ በትክክል ከተወሰደ፣ በሰውነትዎ ውስጥ ያለውን የቫይረስ መጠን የሚቀንስ እና HIV ያለበት ሰው ረጅም እድሜ እንዲኖር የሚያደርግ መድሃኒት አለ። በደንብ ቁጥጥር የተደረገበት የ HIV ኢንፌክሽን ህክምና ካለዎት በግብረ ስጋ ግንኙነት በኩል የመዛመት ስጋት ምንም የለም። ምንም እንኳን ህክምናዎ በደንብ ቁጥጥር የተደረገበት ቢሆንም እንኳን የ HIV ኢንፌክሽንን ሙሉ ለሙሉ ማዳን አይቻልም፣ ቫይረሱም በሰውነትዎ ውስጥ ይቆያል።

### HIV እንዴት ነው የሚተላለፈው?

ብዙ HIV ያለባቸው ሰዎች ልቅ በሆነ የግብረ ስጋ ግንኙነት አማካኝነት የተያዙ ሲሆን፣ አብዛኛውን ጊዜ በእምስ ወይም በቂጥ በኩል በሚደረግ ግንኙነት፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በአፍ በሚደረግ ግንኙነት ይተላለፋል። HIV ያለው ደም ተዛማች ነው እና HIV ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው በደው ዝውውር ወቅት፣ በመርፌ ጫፍ በሚመጣ ጉዳት ወይም ተመሳሳይ መርፌ በመጋራት ሊተላፍ ይችላል። በደንብ ቁጥጥር የተደረገበት HIV ህክምና ላይ፣ በደም ውስጥ ያለው የቫይረስ መጠን በጣም ከማነሱ የተነሳ በግብረ ስጋ ግንኙነት አማካኝነት በሽታው አይተላለፍም። በደም በኩል በሚሆን ኢንፌክሽን (ይህም፣ በመርፌ ጫፍ ጉዳቶች፣ በስለት መቆረጥ እና መርፌ መጋራት)፣ በደንብ ቁጥጥር የተደረገበት ህክምና ከሚከታተል ሰው የመያዝ ስጋት በደንብ የተጠና አይደለም እና ሙሉ ለሙሉ አይተላለፍም ብሎ መወሰን አይቻልም። HIV እናት ወደ ልጅ በእርግዝና ወቅት፣ በወሊድ እና በጡት ማጥባት ጊዜ ሊተላለፍ ይችላል። የእናትየው የ HIV ኢንፌክሽን ቀድሞ ከታወቀ መድሃኒት በመጠቀም ወይም ጡት ማጥባት በመቆጠብ ሙሉ ለሙሉ ልጁ ላይ የሚመጣውን ስጋት ማስወገድ ይቻላል።

**HIV መቼ ነው የማይተላለፈው?**
HIV በመተቃቀፍ፣ በመሳሳም ወይም በመተሻሸት አይተላለፍም። ደም የሌለባቸው እንባ፣ ሽንት፣ ሰገራ፣ ትውከት እና ንፍጥ ቫይረሱን አያስተላልፉም። ምንም ያልተቆረጠ ወይም ጉዳት ያልደረሰበት ቆዳ ጋር የተነካካ ደም ምንም የኢንፌክሽን ስጋት የለውም።

**መብቶች**
በስዊድን ውስጥ እንዳለው Smittskyddslagen መሰረት፣ ምርመራ፣ የክሊኒክ ጉብኝቶች እና የ HIV ህክምናዎች ሁሉም በነጻ የሚሰጡ ናቸው።
ህክመምዎን ማስተዳደር እንዲችሉ ሳይኮ-ሶሺያል እገዛ ማግኘትም ይችላሉ። ሌሎችን ከኢንፌክሽን እንዴት መከላከል እንደሚችሉ ሃኪምዎ ምክርን ይሰጥዎታል።

**የስራ ህይወት**
የ HIV ኢንፌክሽን በሚማሩት ትምህርት ላይ ወይም በሚሰሩት ስራ ላይ ምንም ተግዳሮትን አያመጣም።

**እርግዝና እና ጡት ማጥባት**
ልጅዎ ላይ ሊከሰት የሚችለውን ስጋት በጣም በመቀነስ እንዴት ማርገዝ እንደሚችሉ እርዳታ ለእርስዎ እና ለአጋርዎ ማግኘት ይችላሉ። ልጁን ለመጠበቅ፣ HIV ያለባቸው እርጉዝ ሴቶች የሚከተሉትን ማድረግና አስፈላጊ የሆኑትን የመከላከል ስራዎች እንዲሰሩ ለጤና እንክብካቤ ሰጪዎ ቀድመው HIV እንዳለባቸው ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል። HIV ያለባቸው ሴቶች ጡት እንዳያጠቡ ይመከራሉ።

**HIV ያለባቸው ህጻናት**
ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ልጆች ስለ በሽታቸው በህክምና ሰጪ ሃኪማቸው እንደ እድሜያቸው የሆነ መረጃ ይሰጣቸዋል። HIV ያለባቸው ህጻናት ልክ እንደ ሌሎች ህጻናት ተመሳሳይ የእንክብካቤ እና የትምህርት ቤት መብት አላቸው ነገር ግን ከግምት ውስጥ የሚገባ ልዩ የሆነ ፍላጎቶች ሊኖራቸው ይችላል። ወላጆች/አሳዳጊዎች ለዚህ መስማማታቸውን የሚሰጡ ከሆነ ህክምና ሰጪ ሃኪምዎ ወይም የተዛማጅ በሽታ ሃኪምዎ ለትምህርት ቤቱ መረጃ ሊሰጥ ይችላል። ልጁ ትምህርት ቤት እንደጀመረ የተማሪውን ጤንነት ማሳወቅ አለብዎ።

**በእምስ፣ በቂጥ እና በአፍ በሚደረግ ግብረ ስጋ ግንኙነት ወቅት ኮንዶምን መጠቀም**
ኮንዶሞች HIVን ወይም ሌሎች በግብረ ስጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎችን በጥሩ ሁኔታ ይከላከላሉ። የ HIV ህክምናዎ በደንብ ቁጥጥር የተደረገበት ከሆነ፣ ግብረ ስጋ ግንኙነት ወቅት ኮንዶም እንዲያደርጉ አይገደዱም፣ ነገር ግን ከሌሎች ተላላፊ በሽታዎች ለመጠበቅ ማድረግ ይመከራል።

**ደም ሁልጊዜ እንደ ተዛማች መቆጠር አለበት**

- ከደምዎ ጋር የሚገናኝ ማንም ሰው (ቁስልን በማከም ወይም በተመሳሳይ) ጓንት መጠቀም አለበት።
- አንድ ሰው ከደምዎ ጋር ከተገናነ (ለምሳሌ፣ ክፍት ቁስልን በመንካት ወይም የመርፌ ጫፍ ጉዳት ወይም ቢቆረጥ)፣ HIV ኢንፌክሽን ሊያስተላልፉበት እንደሚችሉ እና የኢንፌክሽን ክሊኒክ/ሃኪም በማግኘት ምርመራ ማድረግ እንዳለባቸው መንገር አለብዎ።

**ወደ ሌሎች እንዳያስተላልፉ መከተል ያለብዎ የስነምግባር መመሪያ**

እንደ Smittskyddslagen መሰረት፣ HIV ማህበረሰቡ ላይ አደጋ የሚያመጣ በሽታ እንደሆነ ተቀምጧል። ስለዚህም ኢንፌክሽኑ ከእርስዎ ወደ ሌላ ሰው እንዳይተላለፍ መከላከል ግዴታ አለብዎ። የኢንፌክሽን ስጋት ከተከሰተ፣ ለሌላኛው ሰው ስለ ህመምዎ ማሳወቅ አለብዎ። በህጉ ውስጥ ከተዳሰሱት ጉደዮች አንጻር ከዚህ በታች መከተል የለብዎ የስነምግባር መመሪያዎች ተዘርዝረዋል። እዚህ ውስጥ ያሉት አብዛኞቹ ህጎች HIV ላለባቸው ሁሉም ሰዎች የሚሆኑ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ግን እንደ ሁኔታዎ ሊለያዩ እና በጊዜ ሂደት ሊቀየሩ የሚችሉ ናቸው። ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ውስጥ የትኞቹ ለእርስዎ እንደሚተገበሩ የሚወስነው የእርስዎ ሃኪም ነው።

1. ደም መለገስ፣ የሰውነት ክፍል ወይም ቲሹ ለንቅለተከላ መስጠት አይችሉም።
2. ለህክምና አላማ መርፌ፣ ካኑላ ወይም ሌላ መውጊያ መሳሪያ የሚጠቀሙ ከሆነ፣ ሌሎች ያንን መሳሪያ እንዲጠቀሙ አይፍቀዱ።
3. እጾችን ወይም ተመሳሳይ ንጥረነገሮችን ለመውጋት መርፋ ወይም ካኑላ ከተጠቀሙ፣ ሌሎች ያንን መሳሪያ እንዲጠቀሙ አይፍቀዱ። የሚጋራ ማደባለቂያ ኩባያም አይጠቀሙ። ሁሉም መውጊያ መሳሪያዎች መቀመጥ ወይም መወገድ ያለባቸው ለሌሎች ስጋት በማያመጡበት መንገድ ነው።
4. የጤና እንክብካቤ ሰጪ ወይም የጥርስ ሃኪም ሲጎበኙ፣ በመርፌ የሚሰጥ ህክምና ወይም ምንም መቁረጥ ሳይከናወን በፊት በደም የሚዛመት በሽታ እንዳለብዎ ማሳወቅ አለብዎ፤ ለምሳሌ፣ ቀዶ ጥገና። እንደዚህ አይነት በየጊዜው ከዋና ጤና እንክብካቤ ሰጪዎ ወይም ከጥርስ ሃኪምዎ ጋር በሚኖሩ ምርመራዎች፣ የደም ናሙና እና መርፌ መውጋቶችን ጨምሮ፣ ይህን መረጃ እንዲያሳውቁ አይጠበቅብዎትም።
5. ባኞ ቤት የሚጠቀሙባቸውን ስለት ያለባቸው እንደ መላጫ የመሳሰሉ እቃዎችን አያጋሩ።
6. ሃክምዎ አስፈላጊ ነው ብሉ የሚያምንባቸውን ህክምናዎች ሁሉ መውሰድ አለብዎ።

እነዚህ የስነምግባር መመሪያዎች ለእርስዎ እንደማይተገበሩ የሚያምኑ ከሆነ በሃገርዎ/በአካባቢዎ ያሉ የተዛማጅ በሽታ ሃኪምን ማግኘት ይችላሉ።